# የሰለጠነ ፖለቲካ

በዘር ሀረግ ሚዛን መስፈርት የተለካ

በጠባብ ጎጥ ስሜት አዚም የተነካ

ከበላባይነት የጠበቀ ሽርካ

ግንኙነት ፈጥሮ ስልጡን ፖለቲካ

ፍርፋሪ ለምዶ የፈረንጅ ቡችላ

ጧፍ ይዞ በመቆም ጌታ ራት ሲያበላ

ልሀጩን ሲያዝራ ጭራውን ሲቆላ

ባንዳነቱ ደምቆ ክህደቱ እየጎላ

ውርደት ተከናንቦ የሁዋላ የሁዋላ

እንደ ጥጥ አቅማዳ አድሮ እየቀለለ

ከትግሉ ይወጣል እየተነጠለ።

ግልፅነት የሚለው ቃል ከሰው ተውሶ

እራሱ ተኩላ የበግ ለምድ ለብሶ

ስልጡን ፖለቲካ ተጠያቂነትን

ቅቤ አንጓች ምላሱ ደፍሮ ግልፅነትን

በጌቶቹ ዘይቤ ቅኝት ተቀኝቶ

ተፍተፍ የሚለው ከመሬት ተነስቶ

አስመሳዩ ሁሉ ማንን ማን አታሎ

ማንን ለማጥፋት ነው በማን አስገድሎ ?

የፈረንጅ ቡችላ

ጭራውን ሲቆላ

ትዝብቱን ሲበላ ቅርሻቱን አዙሮ

ህዝብ ይላል ወቸው ጉድ አገር ተጠራጥሮ

እናታለም ጠኑ.....

ክህደት ነው ዘመኑ......

አገር ከሚሸጡት እየሰለጠኑ

እጅግ ይመረጣል ባላገር መሆኑ

እናም ፋራ እንባል እስከ መጨረሿ

በያነኪ ቡችላ በወያኔ ውሻ!!!!!

ሚያዚያ 2000

Abraham Beyenne